## አጀንዳ ቁጥር 5

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፖለቲካ ትግል ( የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ) አኳያ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጐን መገምገም

የውይይት መድረኩ ከዚህ በላይ የቀረበውን አጀንዳ ለመገምገም ባደረገው ሙከራ በቅድሚያ እስካሁን ውይይት ከተደረገባቸው ሌሎች አጀንዳዎች በበለጠ ይኸኛው አጀንዳ ለግምገማ አስቸጋሪ የሆነ ባህሪ ያለው መሆኑን አስምሮበታል፡፡ ይኸውም- የኢትዮጵያ ሕዝብ በውስጡ በርካታ የአንድነቱና የእርስ በርስ ትስስሩ መገለጫ የሆኑ ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል - በዚያው መጠን በባህል፣ በቋንቋ፣ በእምነት፣ በአስተሳሰብ ደረጃና በኢኮኖሚ አቅም በውስጡ በርካታ ልዩነቶችን ያካተተ /Heterogeneous/ ሕዝብ በመሆኑ ምክኒያት የአጠቃላዩን ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ በተገቢ መጠን ሊያሳይ የሚችል ግምገማ በዚህ አይነቱ የውይይት መድረክ ላይ ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ተገንዝቧል:: ይህንን ግንዛቤ ታሣቢ በማድረግም የውይይት መድረኩ የአብዛኛው ሕዝብና የፖለቲካ ልሂቅ (elite) አጠቃላይ መገለጫ የሆኑ ጥቅል ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ በአጀንዳው ላይ የሚከተለውን ግምገማ ለማድረግ ሞክሯል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አንድ የረዥም ዘመን የመንግሥትነት ታሪክ ያለው ሕዝብ በብዙ ውጣ ውረዶች ተፈትኖ ያለፈና የብዙ በጐና አኩሪ ታሪኮች ባለቤት ለመሆን የበቃ ታላቅ ሕዝብ ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ በጐ የታሪክ ገፅታው በተፃፃሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ከመገንባትና ድህነትን ከማሸነፍ አንፃር ከፍተኛ ድክመት የሚታይበት ሕዝብ መሆኑን የወቅቱ የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ በግሃድ እንደሚያሳይ ግምገማው አምኖበታል፡፡

ከፖለቲካ ትግል ወይንም ከዴምክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር በተያያዘ በሕዝባችን ውስጥ የሚታየውን አወንታዊና አሉታዊ ሁኔታ ብቻ ለይቶ ለመገምገም የሞከረው የውይይት መድረክ - በሕዝባችን ውስጥ በአንፃራዊነት የሚታየው የህግ ተገዥነትና የህግ አክባሪነት፣ የአገርና ታሪክ ወዳድነት፣ የኃይማኖትና የባህላዊ እሴት ቀናኢነት፣ የማህበራዊ ትስስርና የሰላም ወዳድነት ባህሪዎቹ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባት አጋዥ የሚሆኑ የህብረተሰባችን በጐ (አዎንታዊ) ጐኖች መሆናቸው በግምገማው ተጠቅሷል፡፡

ነገር ግን የአገሪቱ ሕዝብ ለረዥም ጊዜ በእርስ-በርስ የጦርነትና የቅራኔ ሂደት ውስጥ ያለፈ፣ የተለያዩ አምባገነናዊና ጨቋኝ መንግሥታት ሲፈራረቁበት የኖረ፣ አብዛኛውም ሕዝብ የዘመናዊ ትምህርት እድል ያላገኘና በኢኮኖሚ አቅሙም መሠረታዊ ፍላጐቱን ገና ያላሟላ ሕዝብ በመሆኑ ምክኒያት በአሁኑ ወቅት የሚገኝበት የሶሺዮ-ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በቀላሉ ለመገንባት እንዳላስቻለው ግምገማው አመላክቷል፡፡ ከአጠቃላዩ ሕዝብ 85% የሚሆነው ሕዝብ በጉርስ እርሻ (Subsistence Agriculture) ተዳዳሪ በሆነበትና በዚያው መጠን አብዛኛው ሕዝብ መሃይም በሆነበት ሁኔታ በአንድ አገር ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የሚሆን መካከለኛ ገቢ ያለው /middle class/ የህብረተሰብ ክፍል በቀላሉ ሊፈጠር እንደማይችል የጠቆመው ግምገማ - በየደረጃው የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትና ችግር ፈች የሆነ

የትምህርት ሥርዓት በፍጥነት እስካልተስፋፋ ድረስ በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እጅግ አዝጋሚ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችል ያለውን ግምት አስቀምጧል።

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ወይንም የሰከነ የፖለቲካ ትግል ባህልን ለመገንባት ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የህብረተሰብ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ - ከላይ በበጐ ጐንነት የተጠቀሱ የሕዝባችን ባህሪዎችን በአግባቡ በመጠቀም የአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ቢያንስ አዝጋሚም በሆነ መጠን የሚገባውን ያህል እንዳይጠናከር እንቅፋት በመሆን እረገድ የሚከተሉት ምክኒያቶች ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ግምገማው አሳይቷል።

በግምገማው ወቅት ከተጠቀሱት ምክኒያቶች ውስጥ -በአገራችን ለሰላማዊ ትግልና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የመሪነት ሚናውን በአግባቡ ሊጫወት የሚችል ብቃት ያለው የፖለቲካ ልሂቅ ሊፈጠር አለመቻሉ ዋነኛው ምክኒያት መሆኑ ተጠቁሟል። ሕዝቡ የራሱን የፖለቲካ መሪዎች በመፍጠር እረገድ የማይተካ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና ያለው ቢሆንም ዞሮ ዞሮ በአሁኑ ዘመን የትግሉ ግንባር ቀደም መሪ ሊሆን የሚገባው የፖለቲካ ልሂቅ የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታና የፖለቲካ ቅራኔዎች በአግባቡ መተንተንና መፍትሔ ማመንጨት የሚችል የአስተሳሰብ ታላቅነት ያለው ኃይል ሊሆን ባለመቻሉ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገው የፖለቲካ ትግል የሚገባውን ያህል ስክነትና ብስለት ሊያሳይ አልቻለም። የዚህ ዓይነት ከፍተኛ የአመራር ክፍተት በመኖሩ ምክኒያትም ለአገሪቱ መድህን የሚሆን ብሔራዊ ራዕይ መፍጠር እንዳልተቻለና በሕዝቡ ውስጥም ለዘመናት ተንሰራፍተው የኖሩ የአረጁ አስተሳሰቦችንም በሚገባው መጠንና ፍጥነት በአዲስና ገንቢ አስተሳሰብ እስካሁን መተካት እንዳልተቻለ -፣ ለዚህም ዋናው ተጠያቂ የአገሪቱ የፖለቲካ ልሂቅ እንደሆነ ታምኖበታል።

የአገሪቱ የፖለቲካ ልሂቅ በሚፈለገው መጠን የጠራ አገር ጠቀም አስተሳሰብና ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ፈጥሮ የአገሪቱን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ትክክለኛ አቅጣጫ እስካልያዘ ድረስ በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩትን አሉታዊ አስተሳሰቦች መለወጥ በራሱ አስቸጋሪ ጉዳይ ቢሆንም - በተመሳሳይ ሁኔታ በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩት አሉታዊ አስተሳሰቦች ጥልቅና ውስብስብ መሆናቸው ለጠንካራ የፖለቲካ ልሂቅ አለመፈጠር ዋነኛ ምክኒያት ሆነው እናገኛቸዋለን። ከፖለቲካ ትግሉ ሂደት ጋር በተያያዘ በሕዝባችን ውስጥ ጐልተው የሚታዩት የጨለምተኝነት፣ የጥላቻ፣ የጥንፈኝነት፣ የተጠራጣሪነት፣ የአሉባልተኝነትና የተስፋ ቆራጭነት ባህሪዎች በአገራችን ብቃት ያለው የፖለቲካ ልሂቅ እንዳይፈጠር ከራሱ ከፖለቲካ ልሂቁ ደካማ ባህሪዎች ጋር እርስ በርስ ተመጋጋቢ የሆነ መሰናክል እንደፈጠሩ ግመገማው አሳይቷል።

ከእነዚህ አይነቶቹ አሉታዊ ባህሪዎች በተጨማሪ በሕዝባችን ውስጥ የሚታዩት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አስተሳሰቦች በአሁኑ ወቅት ለፖለቲካ ትግሉ አለመጠናከር ተጨማሪ ምክኒያቶች እንደሆኑ ታምኖበታል።

እነርሱም-

- በፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ በተለያየ የጥቅም አስከባሪ ሲቪል ማህበራት ዙሪያ የመደራጀትን አስፈላጊነት ያለመገንዘብና በጉልበት፣ በእውቀት፣ በጊዜና በገንዘብ ከራስ የሚጠበቅን አስተዋፅኦ መወጣት አለመቻል፤

- ፖለቲካ የራስን፣ የመጭውን ትውልድና በአጠቃላይም የአገርና የሕዝብን እጣ ፈንታ የሚወስን ታላቅ ቁምነገር መሆኑን አለመገንዘብና በተዛባ መንገድ ፖለቲካን "ኮረንቲ" እና "ቆሻሻ" ተግባር አድርጐ መመልከት፤

- ዴሞክራሲ የብዙ መብቶች መገለጫና መገኛ የመሆኑን ያህል በዚያው መጠን እንደየ ህብረተሰቡ የሶሺዮ -ኢኮኖሚ ወቅታዊ ሁኔታ አስፈላጊ ገደቦች ሊጣሉበት የሚችልና ግዴታዎችንም በሌሎች ላይ ሊያስከትል የሚችል የፖለቲካ ሥርዓት መሆኑን አለመገንዘብ፤

- በሰላማዊ ትግል ውጤታማነት ላይ ሙሉ እምነት አለማሳደርና ከመንግሥት በኩል ተፅእኖዎች ጠንከር ብለው በተቃጡ ቁጥር የትጥቅ ትግልን እንደአማራጭ ስልት ማየትና ሠላማዊ ትግልን እንደ ከንቱ ድካም መቁጠር፤

- በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት በአግባቡ ሳያጤኑ በጥቅል እንደ አንድ የፖለቲካ ኃይል ማየትና ተገቢ ያልሆነ ህብረትና አንድነት እንዲፈጥሩ አላስፈላጊ ግፊት ማድረግ፣

- የአገሪቱ ችግሮች መንስኤም ሆነ መፍትሔ መንግሥት ብቻ እንደሆነ አድርጐ ማሰብ፤

- በአገሪቱ ግብታዊ የሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ለውጥ እንዲመጣ መጠበቅ፣

- የተሻለ ለውጥ የመምጣትን ጉዳይ በዋናነት ከመንግሥት ለውጥ ጋር አያይዞ ማየት፤

- እራስን የአገሪቱ ችግሮችና መፍትሔዎች አካል አድርጐ ካለማየት በመነጨ ለአገሪቱ ችግሮች ሌሎችን ብቻ ተጠያቂ ማድረግና የሚፈለገውንም ለውጥ ከሌሎች መጠበቅ፤

- የፖለቲካ መሪዎችንና ድርጅቶችን ከራስና ከአገር ትክክለኛ ጥቅም አኳያ ከመገምገም ይልቅ ስሜታዊና ጊዜያዊ (populist) በሆኑ ምክኒያቶች መደገፍና መቃወም፤

- ግላዊና አካባቢያዊ ጥቅምና ፍላጐትን ከአጠቃላዩ ሕዝብና ከአገር ጥቅም ጋር በሚዛናዊነት ማቻቻል አለመቻል፤

- ስለአገሪቱ ታሪክ፣ ስለአገር ፍቅርና ስለጀግንነት ትርጉም ያልጠሩና የተዛቡ አመለካከቶችን ማራመድ፤

- ከራስ ኃይማኖት፣ ብሔረሰብዓዊ ማንነትና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አኳያ በመነሳት ብቻ የአገሪቱን ችግሮች ያለአግባብ አቃሎ ወይንም ያለአግባብ አወሳስቦ

መመልከትና እራስን በሌሎች ቦታ አስቀምጦ የአገሪቱን ችግሮች በሚዛናዊነት ለመረዳት አለመሞከር፤

❖ የተማሩ ሰዎችን ሁሉ የአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳይ አዋቂዎችና ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ከማንም በላይ ተቆርቋሪ ዜጎች እንደሆኑ አድርጐ ያለአግባብ ማምለክ፣

❖ በአጠቃላይ የፖለቲካ ኃይሎችን በጭፍን በመደገፍና በጭፍን በመቃወም ምክኒያታዊ ያልሆነ ጥንፈኛ የፖለቲካ ስልት ማራመድ የፖለቲካ ትግሉን መጠናከር እያሰናከሉ የሚገኙ አሉታዊ የሕዝብ አስተሳሰቦች መሆናቸው ታምኖበታል፡፡

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ በህብረተሰባችን ውስጥ የሚታዩ አሉታዊ አስተሳሰቦች ለወቅቱ የፖለቲካ ባህላችን ደካማ ወይንም ብልሹ መሆን መሠረታዊ ምክኒያቶች ቢሆኑም አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እስካሁን ለእነዚህ በራሱ ውስጥ ለሚገኙ ችግሮች ተገቢውን እውቅና ባለመስጠት የአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች የመንግሥት ሥልጣን ከያዙ የፖለቲካ ኃይሎች ብቻ የሚመነጩ እንደሆነ አድርጐ እንደሚመለከት ግምገማው ጠቁሟል፡፡

የአገራችን ፖለቲካ ከእነዚህ ችግሮች ተላቆ ወደ ላቀ ደረጃ በሂደት ይሸጋገር ዘንድም - በአንድ በኩል የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነው ሕዝቡና የፖለቲካ ትግሉን ተገቢ አቅጣጫ አስይዞ መምራት የሚገባው የአገራችን የፖለቲካ ልሂቅ ለእነዚህ ችግሮችና ድክመቶች ተገቢውን እውቅናና ትኩረት ሰጥቶ ችግሮቹን ለመፍታት መታገል ከቻለ፣ በሌላ በኩልና በዋናነት ደግሞ ትምህርትንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በማፋጠን የህብረተሰቡን የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ መለወጥ ከተቻለ ዴምክራሲያዊ ህብረተሰብና አገር ያለጥርጥር በዘላቂነት መፍጠር እንደሚቻል ግምገማው አምኖበታል፡፡

ሕዝባችንም ሆነ የአገራችን የፖለቲካ ልሂቅ የአገራችንን የፖለቲካ ችግር ከዚህ አንፃር ማየት ካልቻሉና እንደ እስካሁኑ ለአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች መንግሥትን ብቸኛ ተጠያቂና መፍትሔ አመንጭ አድርገው ማየት የሚቀጥሉ ከሆነ ግን የአገራችን የፖለቲካ ችግሮች ከመቃለል ይልቅ ይበልጥ እየተባባሱ ሊሄዱ እንደሚችሉና አገራችንም ለተጨማሪ ብዙ አመታት በአንድ ፓርቲ የበላይነት አየተገዛች ልትቀጥል እንደምትችል ግምገማው የሚሰማውን ስጋት ገልጾ ተጠናቋል፡፡